የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

# የኮቪድ-19 ክትባት መረጃ ወረቀት

ስሪት 5.0 – ኢፕሪል 1፥ 2021 ዓ.ም.

ይህ ሰነድ መሠረታዊ መረጃ ብቻ የሚሰጥ ሲሆን፥ በሕክምና ምክር፥ በምርመራ ወይም በሕክምና ቦታ ወይም በሕጋዊ ምክር ምትክ እንዲወሰድ ታቅዶ የቀረበ አይደለም።

እስከዛሬ የሚከተሉት የኮቪድ-19 ክትባቶች በካናዳ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በHealth Canada (የካናዳ ጤና ሚኒስቴር) ፈቃድ ተሰጥቷቸዋል፦ Pfizer-BioNTech (ፋይዘር-ባዮኤንቴክ) የኮቪድ-19 ክትባት፥ Moderna (ሞዴርና) የኮቪድ-19 ክትባት፥ AstraZeneca (አስትራዜኔካ) ኮቪድ-19 ክትባት፥ COVISHIELD (ኮቪሺልድ) የኮቪድ-19 ክትባት እና Janssen (ጃንሰን) ኮቪድ-19 ክትባት። ለካናዳ ያለው አቅርቦት ከተረጋገጠ በኋላ፥ ስለ Janssen ኮቪድ-19 ክትባት መረጃ እዚህ ሰነድ ላይ ይጨመራል። በካናዳ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ፈቃድ የተሰጣቸው ሁሉም vaccines for COVID-19 የኮቪድ-19 ክትባቶች ጥብቅ ደረጃዎችን በመጠቀም በ Health Canada የተገመገሙ ናቸው። Health Canada ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑንና ውጤታማ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ክትባቶችን ሁሉ መከታተሉን ይቀጥላል።

**እባክዎን ይህንን መረጃ ወረቀት በጥንቃቄ ያንብቡና ክትባቱን ከመውሰድዎ በፊት ለጥያቄዎችዎ በሙሉ ከሕክምና አገልግሎት ሰጪ መልስ ማግኘትዎን ያረጋግጡ።**

## ኮቪድ-19 ምንድነው?

ኮቪድ-19 በአዲስ ኮሮናቫይረስ (SARS-CoV-2) ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው። ኮቪድ-19 ለመጀመሪያ ጊዜ የታወቀው በዲሴምበር 2019 ዓ.ም. ሲሆን፥ ከዚያ ወዲህ በዓለም ላይ ሁሉ ተሠራጭቶ ወረርሽኝ አስከትሏል። ኮቪድ-19 በዋናነት በበሽታው ከተያዘ ሰው ወደሌሎች የሚሠራጨው የተያዘው ሰው ሲስል፥ ሲያስነጥስ፥ ሲዘፍን፥ ሲያወራ ወይም ሲተነፍስ ነው። በበሽታው የተጠቁ ሰዎች ምንም ምልክት ባይኖራቸውም በሽታውን ማስተላለፍ እንደሚችሉ መገንዘቡ አስፈላጊ ነው። Symptoms of COVID-19የኮቪድ-19 ምልክቶች ሳል፥ የትንፋሽ እጥረት፥ ትኩሳት፥ ብርድ ብርድ ማለት፥ ድካም፥ የሽታ ወይም የጣዕም እጦት ሊያካትቱ ይችላሉ። አንዳንድ በቫይረሱ የተጠቁ ሰዎች ምንም ዓይነት የሕመም ምልክት አያሳዩም፥ ሌሎች ደግሞ ከቀላል እስከ ከባድ ሕመም ሊያጋጥማቸው ይችላል።

### የኮቪድ-19 ክትባቶች ከኮቪድ-19 የሚከላከሉት እንዴት ነው?

ክትባቶች ሁሉ የሚሠሩት የሰውነታችን በሽታ የመከላከል ሥርዓት ተፈጥሯዊ ጥበቃን እንዴት ማምጣት እንደሚችል መማር እንዲችል ለሰውነታችን በሽታውን የሚመስል ነገር በማቅረብ ነው። ወደፊት የኮቪድ-19 ቫይረስ ቢያጋጥምዎት ይህ ተፈጥሯዊ ጥበቃ በሽታን ለመከላከል ይረዳል። **ኮቪድ-19 ከክትባቱ ሊይዝዎት አይችልም።**

የኮቪድ-19 ክትባቶች እንዴት ጥበቃ እንደሚሰጡ የሚገልጽ የበለጠ ዝርዝር መረጃ በ Public Health Ontario's (PHO) (የኦንታሪዮ ጤና ጥበቃ) ኮቪድ-19 ክትባቶች ድህረገጽ እና ስለ ኮቪድ-19 ክትባት ማወቅ ያለብዎት እና የኮቪድ-19 ክትባቶች፦በቫይራል ቬክተር ላይ የተመሠረቱ ክትባቶች ላይ ይገኛል።

**በካናዳ ውስጥ ፈቃድ የተሰጣቸው የኮቪድ-19 ክትባቶች ሁሉ ከምልክታዊ፥ በላቦራቶሪ ከተረጋገጠ በሽታ ሁሉ በመጠበቅ ውጤታማ ናቸው።** ሰዎች ሁለቱንም ክትባቶች ባገኙባቸው ሰፊ ጥናቶች ውስጥ እንደታየው፥ ክትባቶች ሁሉ ሰዎችን ከምልክታዊ፥ በላቦራቶሪ ከተረጋገጠ ኮቪድ-19 ሕመም በመጠበቅ በሚገባ ሠርተዋል። የመጀመሪያው ክትባት ከተወሰደ ከ14 ቀናት በኋላና ሁለተኛው ክትባት ከመወሰዱ በፊት ያለው የPfizer-BioNTech እና የ Moderna ክትባት ውጤታማነት ከ90% በላይ ሲሆን የAstraZeneca/COVISHIELD ደግሞ ከ70% በላይ ነው። በሚመከረው ጊዜ ሁለተኛውን ክትባት ከወሰዱ በኋላ የPfizer-BioNTech እና የ Moderna ክትባት ውጤታማነት ከ90% በላይ ሲሆን የAstraZeneca/COVISHIELD ደግሞ ከ80% በላይ ነው። የእነዚህን ክትባቶች ሁለት ዙር መውሰድዎ አስፈላጊ ነው። ሁለተኛው የክትባት ዙር ካልተወሰደ ከኮቪድ-19 ዘለቄታዊ ጥበቃ ማግኘት አይቻልም። **ሁሉም የኮቪድ-19 ክትባቶች በካናዳ ውስጥ ጥቅም ላይ ለመዋል ፈቃድ ያገኙ ሲሆን ሆስፒታል ከመተኛት መከላከል ላይ በጣም ውጤታማ ናቸው።**

## እነዚህን ክትባቶች ማግኘት የሚችለው ማነው?

ከክትባቱ ጋር ሊጣሉ የሚችሉ ሁኔታዎች የሌሏቸውና ባሁኑ ወቅት ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ተለይተው የታወቁ ሰዎች ሙሉ ተከታታይ ክትባቶችን እንዲያገኙ ሊቀርብላቸው ይገባል።

- ባሁኑ ጊዜ የPfizer-BioNTech ኮቪድ-19 ክትባት ዕድሜያቸው 16 እና ከዛ በላይ ለሆኑ ግለሰቦች ተፈቅዷል።
- ባሁኑ ጊዜ የModerna ኮቪድ-19 ክትባት ዕድሜያቸው 18 እና ከዛ በላይ ለሆኑ ግለሰቦች ተፈቅዷል።
- ባሁኑ ጊዜ የAstraZeneca እና የCOVISHIELD ኮቪድ-19 ክትባት ዕድሜያቸው 18 እና ከዛ በላይ ለሆኑ ግለሰቦች ተፈቅዷል። ባሁኑ ጊዜ National Advisory Committee on Immunization (NACI) (ብሔራዊ የክትባት አማካሪ ኮሚቴ) የAstraZeneca ኮቪድ-19 ክትባትና COVISHIELD ዕድሜያቸው ከ55 ዓመት በታች የሆኑ አዋቂዎች እንዳይከተቡት ) recommendsይመክራል።

ባሁኑ ጊዜ ክትባቱን ለመውሰድ ቅድሚያ እንዳልዎት ለማወቅ የኦንታሪዮ ኮቪድ-19 ክትባት ዕቅድን ይጎብኙ።

### ክትባቱን ከመውሰድዎ በፊት የሚከተሉት ተከስተው ከሆነ ክትባቱን ለሚሰጥዎ የሕክምና አገልግሎት ሰጪ ያሳውቁት:-

- ባሁኑ ወቅት ጤንነት አይሰማዎትም ወይም የኮቪድ-19 ምልክቶች አሉብዎት።
- ከዚህ በፊት የኮቪድ-19 ክትባት ሲወስዱ ወይም የኮቪድ-19 ክትባቶች ውስጥ ወይም ሌላ ክትባት ውስጥ ያሉት ንጥረነገሮች የአለርጂ ችግር አምጥቶብዎት ከነበረ።
- ማንኛውም ዓይነት የአለርጂ ችግር ካለብዎት።
- ነፍሰ ጡር ከሆኑ ወይም ሊሆኑ የሚችሉ ከሆነ ወይም ጡት እያጠቡ ከሆነ።
- በሕመም ወይም በሕክምና ምክንያት የሰውነት መቋቋም ዓቅምዎ የተዳከመ ከሆነ ወይም የተፈጥሮ በሽታ የመከላከል ዓቅምን የሚያጠቃ በሽታ ካለብዎት።
- ከዚህ በፊት ክትባት ከወሰዱ በኋላ ወይም ሕክምና ከተደረገልዎት በኋላ ራስዎን ከሳቱ ወይም ካዞርዎት ወይም የመርፌ ፍርሃት ካለብዎት። የሕክምና አገልግሎት ሰጪው ድጋፍ ሊሰጥዎ ይችላል፥ ለምሳሌ ራስዎን ስተው እንዳይወድቁ ክትባቱን ጋደም ብለው እንዲወስዱ ሊያደርግ ይችላል።
- ደም የመፍሰስ በሽታ ካለብዎት ወይም ደም መርጋት ላይ ተጽዕኖ ሊያስከትል የሚችል መድኃኒት እየወሰዱ ከሆነ። ይህ መረጃ የሕክምና አገልግሎት ሰጪው ከመርፌ መወጋት ደም መፍሰስ ወይም መቁሰል እንዳይከተል ሊጠነቀቅ ይችላል።
- ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ማንኛውም ዓይነት ሌላ ክትባት (ከኮቪድ-19 ሌላ) ወስደዋል።

ለልዩ ሕዝቦች የክትባት ምክሮች መመሪያ ሰነድ ጡት እያጠቡ ላሉ ወይም ነፍሰጡር ለሆኑ፥ የአለርጂ ችግር ላላቸው፥ የተፈጥሮ በሽታ የመከላከል ዓቅምን የሚያጠቃ ሕመም ላለባቸው ወይም በበሽታ ወይም በሕክምና ምክንያት የሰውነታቸው መቋቋሚያ አቅሙ ደካማ ለሆኑ እንዲሁም በበሽታ ወይም በኮቪድ-19 ምክንያት ከባድ ችግር ሊያጋጥማቸው ለሚችሉ ጎረምሶች ተጨማሪ መረጃ ያቀርባል። በጤና ችግር ምክንያት ክትባቱ ለእርስዎ ተስማሚ መሆኑን በተመለከተ ጥያቄዎች ካሉዎት የሕክምና አገልግሎት ሰጪዎን ያነጋግሩ።

## እነዚህን ክትባቶች ከመውሰድ መዘግየት ያለበት ማን ነው?

- ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ሌላ ክትባት (ከኮቪድ-19 ክትባት ሌላ) የወሰዱ ግለሰቦች።
- የከባድ ሕመም ምልክቶች ያሏቸው ግለሰቦች፥ ከክትባቱ ጋር የተያያዙ ጎጂ ጎኖች ጋር ማገናኘትን ለማስወገድ እነዚህ ግለሰቦች የሕመም ምልክቶቻቸው ሙሉ በሙሉ እስከሚጠፉ መጠበቅ አለባቸው።
- የኮቪድ-19 ምልክቶች ያሏቸው ግለሰቦች። ኮቪድ-19 የማጋባት ዕድልን ለመቀነስ፥ እነዚህ ግለሰቦች የክትባት ክሊኒክ/ቦታ ሲደርሱ ወቅታዊ የአካባቢውን የጤና አጠባበቅ እርምጃዎች እንዲከተሉ መመሪያ ተሰጥቷቸው ምርመራ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ።
- ኮቪድ-19 እንዳለባቸው የተጠረጠሩና የተረጋገጠላቸው ወይም ኮቪድ-19 የያዘው ሰው አካባቢ በቅርብ የነበሩ የሕመም ምልክት የሚያሳዩ እና የማያሳዩ ራሳቸውን እንዲያገሉ የተመከሩ ግለሰቦች የክትባት ክሊኒክ መሄድ የለባቸውም፥ ክትባታቸውንም ለመውሰድ የመገለል ጊዜያቸው እስከሚያበቃ ድረስ መቆየት አለባቸው።

## ክትባቱ የሚሰጠው እንዴት ነው?

ክትባቱ የሚሰጠው ክንድ ላይ በመርፌ ነው (የትከሻ ጡንቻ ላይ)። ለ Pfizer-BioNTech፥ Moderna እና AstraZeneca/COVISHIELD ክትባቶች፥ የመጀመሪያው ዙር ከተሰጠ በኋላ ክፍለ ሐገሩ ሁለተኛው የኮቪድ-19 ክትባት ዙር የሚሰጥበትን ጊዜ እስከ 4 ወር ድረስ ለማራዘም የ National Advisory Committee on Immunication (NACI)ን ጥቆማዎች እየተከተለ ነው።

- ለPfizer-BioNTech ክትባት፥ የመጀመሪያው ዙር ከተወሰደ በኋላ በአንደኛውና በሁለተኛው ክትባቶች መካከል የሚመከረው ርቀት 4 ወር ነው።
- ለModerna ክትባት፥ የመጀመሪያው ዙር ከተወሰደ በኋላ በአንደኛውና በሁለተኛው ክትባቶች መካከል የሚመከረው ርቀት 4 ወር ነው።
- ለAstraZeneca እና COVISHIELD ክትባት የመጀመሪያው ዙር ከተወሰደ በኋላ በአንደኛውና በሁለተኛው ክትባቶች መካከል የሚመከረው ርቀት 4 ወር ነው።

ግለሰቦች የሚወስዷቸው ተከታታይ ክትባቶች በሙሉ ከአንድ ዓይነት ክትባት መሆን አለባቸው (ማለትም አንድ ግለሰብ የሚወስደው አንደኛ ዙርና ሁለተኛ ዙር ክትባት አንድ ዓይነት መሆን አለበት)። የተለያዩ ዓይነት ክትባቶች (ለምሳሌ mRNA፥ ቫይረስ መተላለፊያ መንገድ) የተለያዩ ዓይነት ክትባቶች ተብለው መታየት አለባቸው፥ በተከታታይም ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም።

## የክትባቶቹ ንጥረ ነገሮች ምንድን ናቸው?

| ንጥረ ነገሮች | | Pfizer-BioNTech | Moderna | AstraZeneca/ እና COVISHIELD |
|---|---|---|---|---|
| የሕክምና | | • mRNA | • mRNA | • የማይባዛ ቫይረስ መተላለፊያ መንገድ (ChAd) |
| የሕክምና ያልሆነ | ሊፒዶች | • ALC-0315<br>• ALC-0159 – a polyethylene glycol (PEG)<br>• 1,2-Distearoyl-sn-glycero-3-phosphocholine (DSPC)<br>• ኮሌስትሮል | • 1,2-distearoyl-sn-glycero-3-phosphocholine (DSPC)<br>• ኮሌስትሮል<br>• PEG2000 DMG SM-102 | • Disodium edetate dihydrate (EDTA)<br>• ኤታኖል<br>• L-Histidine<br>• L-Histidine hydrochloride monohydrate<br>• Polysorbate 80 |
| | ጨዎች | • Dibasic sodium phosphate dihydrate<br>• Monobasic potassium phosphate<br>• Potassium chloride<br>• Sodium chloride | • Acetic acid<br>• Sodium acetate trihydrate<br>• Tromethamine<br>• Tromethamine hydrochloride | • Magnesium chloride hexahydrate<br>• Sodium chloride |
| | ስኳር | • Sucrose | • Sucrose | • Sucrose |
| | | • ለመርፌ ውሃ | • ለመርፌ ውሃ | • ለመርፌ ውሃ |

አንዳንድ ሰዎች ለእነዚህ ንጥረ ነገሮች፥ **polyethylene glycol (PEG) (ፖሊኤቲሊን ግላይኮል)፥ polysorbate 80 (ፖሊሶርቤት** 80) እና/ወይም **tromethamine(ትሮሜታሚን)**ን ጨምሮ፥ የአለርጂ ችግር ሊኖርባቸው ስለሚችል ይህንን ዝርዝር በጥንቃቄ ማንበቡ አስፈላጊ ነው። ሆኖም እነዚህ የአለርጂ ችግር ማስከተላቸው ያልተለመደ ነው። Polyethylene glycol (PEG) (ፖሊኤቲሊን ግላይኮል) መድኃኒቶች፥ አንጀትን ለኮሎኖስኮፒ ማዘጋጃ ንጥረ ነገሮች፥ ሆድ ማለስለሻ መድኃኒቶች፥ የሳል ሽሮፖች፥ ኮስሞቲክስ፥ የቆዳ ቅባቶች፥ ቆዳ ላይ እና በቀዶ ጥገና ጊዜ የሚጠቀሟቸው የሕክምና ምርት ውጤቶች፥ የጥርስ ሳሙና፥ በዓይን ብሌን ላይ ተለጣፊ መነጽሮች እና የመነጽሮች

ማጽጃ ፈሳሾች ውስጥ ይገኛል። Polyethylene glycol (ፖሊኤቲሊን ግላይኮል) ምግብ ወይም መጠጦች ውስጥም የሚገኝ ሲሆን ከምግብ ወይም ከመጠጥ የአለርጂ ችግር በማስከተል አይታወቅም። Polysorbate 80 (ፖሊሶርቤት 80) የሕክምና ቅመማዎች (የቫይታሚን ዘይቶች፥ ኪኒኖችና ጸረ-ነቀርሳ ንጥረ ነገሮች) ውስጥ እና ኮስሞቲኮች ውስጥ ይገኛሉ። Tromethamine (ትሮሜታሚን) ደምስሮችን በግልጽ ማሳያ፥ በአፍ ወይም በሌላ መንገድ የሚወሰድ መድኃኒቶች ውስጥ ይገኛል።

# የክትባቱ ጎጂ ጎኖች ምንድን ናቸው?

የኮቪድ-19 ክትባቶች እንደማናቸውም ክትባቶች ጎጂ ጎኖች ሊኖሯቸው ይችላል፥ ሆኖም ሁሉ ሰው ላይ አይከሰቱም ቢከሰቱም አነስተኛ ችግሮች ናቸው። ብዙ ጊዜ የኮቪድ-19 ክትባት ከወሰዱ በኋላ የሚከሰቱ ጎጂ ጎኖች በቦታ የተወሰኑ ሲሆኑ፥ የተወጋው ቦታ ላይ ሕመም፥ መቅላት ወርም እብጠት፥ ድካም ራስ ምታት፥ የጡንቻ ሕመም፥ የመገጣጠሚያ ሕመም፥ ብርድ ብርድ ማለትና መለስተኛ ትኩሳትን ያካትታሉ።

በእነዚህ ኮቪድ-19 ክትባቶች ላይ ቀጣይ ጥናቶች እንደሚያሳዩት እስከዛሬ ድረስ ከባድ ጎጂ ጎን የተከሰተው **እጅግ በጣም ጥቂት** ጊዜ ነው። ክትባት የወሰዱ ሰዎች ዘላቂ ጎጂ ጎን ያጋጥማቸው እንደሆነ ለማየት በእነዚህ ጥናቶች ውስጥ አሁንም ክትትል ይደረግላቸዋል።

ከፍተኛ የአለርጂ ችግር ቢፈጠር የክሊኒክ ሠራተኞች ለማስተናገድ ዝግጅት አድርገዋል። ሁለተኛ ዙር የኮቪድ-19 ክትባት በሚወስዱ ጊዜ፥ **የመጀመሪያውን ዙር ከወሰዱ በኋላ ጎጂ ጎን ኢጋጥመዎት ከነበረ ለሕክምና አገልግሎት አቅራቢው ያሳውቁት።**

በጣም ባልተለመደ ሁኔታ፥ የAstraZeneca/COVISHIELD ክትባት ብዙ ከማይከሰት የደም መርጋት ጋር ተያይዟል። ዶክተሮች ይህንን "vaccine-induced prothrombotic immune thrombocytopenia" (VIPIT) (በክትባት የሚመጣ የደም መርጋት የሚያመጣ ኢምዩን ትሮምቦሲቶፔኒያ) ብለው ይጠሩታል። እነዚህ የደም መርጋቶች ሁለት አስፈላጊ ገጽታ አላቸው፡- ክትባት ከተወሰደ ከ4 እስከ 20 ቀናት በኋላ ነው የሚከሰቱት፥ እንዲሁም ከዝቅተኛ ፕሌትሌት (ደም ሲረጋ እንዳይፈሱ የሚረዱ ጥቃቅን የደም ሴሎች) ጋር የተያያዙ ናቸው። VIPIT በጣም ያልተለመደ ሲሆን ከ125000 ሰዎች ውስጥ 1 ሰው ላይ ወይም ከ1 ሚሊዮን ሰዎች ውስጥ 1 ሰው ላይ ብቻ ነው የሚከሰተው። ዕድሜያቸው ከ55 በታች የሆኑ ሴቶች ላይ ነው በይበልጥ የሚከሰተው። ይበልጥ መረጃ ለማግኘት እባክዎን VIPIT ከኮቪድ-19 ክትባት በኋላን ይጎብኙ።

በዚህ ጉዳይ ላይ Health Canada ግምገማ አካሂዶ AstraZeneca/COVISHIELD ክትባት ካናዳዊዎችን በመጠበቅ ጥቅሙ ከጉዳቱ እንደሚያመዝን ወስኗል። የደም መርጋት በተለይ በአዛውንቶች ላይ የተለመደ ነው። ኮቪድ-19 እራሱ ደም መርጋት ከማስከተል ጋር ተያይዟል፥ ስለዚህ ከዚህ በፊት የደም መርጋት የነበረባቸው ሰዎች ወይም በዘር የደም መርጋት ታሪክ ያላቸውና ደም ማቅጠኛ መድኃኒት የሚወስዱ ሰዎች ማናቸውንም የኮቪድ-19 ክትባቶች እንዲወስዱ ይመከራሉ።

# የሕክምና አገልግሎት ሰጪዬ ጋር መደወል ያለብኝ መቼ ነው?

አሳሳቢ ጎጂ ጎኖች ካጋጠሙዎት ወይም ከትንሽ ቀናት በኋላ የማይሻሉ ከሆነ የሕክምና አገልግሎት ሰጪዎን ይገናኙ ወይም ለሕክምና ይሂዱ።

ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ በሶስት ቀናት ውስጥ የሚከተሉት ነገሮች ከተከሰቱ በቅርብ የሚገኝ **ድንገተኛ ክፍል ጋር ይሂዱ ወይም 911 ይደውሉ፦**

- ሽፍታ
- የፊት ወይም የአፍ እብጠት
- የመተንፈስ ችግር
- ፈዛዛ ቀለም ወይም ከባድ ራስ ማዞር
- ከፍተኛ ትኩሳት (ከ40°C በላይ)
- መንቀጥቀጥ ወይም አዙሪት
- ሌሎች ከባድ ምልክቶች (ለምሳሌ በመርፌ እንደተጠቀጠቁ ዓይነት ስሜት ወይም መደንዘዝ)።

የAstraZeneca/COVISHIELD ክትባት ከወሰዱ በኋላ ከሚከተሉት ውስጥ ማናቸውንም ምልክቶች ካሳዩ **እባክዎን ወዲያውኑ ወደ ሐኪም ይሂዱ፦**

- የትንፋሽ እጥረት
- የደረት ሕመም
- የክንድ ወይም የእግር እብጠት ወይም የቅዝቃዜ ስሜት
- የማያቋርጥ ሆድ ሕመም
- ከባድ ወይም እየባሰ የሚሄድ ራስ ምታት ወይም ብዥ ያለ እይታ
- በርካታ ትናንሽ ቁስሎች፥ ከቆዳ ሥር ቀይ ወይም ሐምራዊ የደም ቋጠሮዎች።

ጥያቄ ለመጠየቅ ወይም ችግር ለማሳወቅ የ አካባቢውን የጤና ጥበቃ ክፍል መገናኘት ይችላሉ።

# ለሁለተኛው ዙር መቼ መመለስ አለብኝ?

ይህ የመጀመሪያዎ የኮቪድ-19 ክትባትዎ ከሆነ የመጀመሪያውን ክትባት የሰጥዎት የክትባት ክሊኒክ ወይም የሕክምና አገልግሎት ሰጪ በሰጠው መመሪያ መሠረት ለሁለተኛው ዙር ተመልሰው መሄድዎን ያረጋግጡ። ሁለቱንም የክትባት ዙር ማግኘቱ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ከኮቪድ-19 የሚገኘው ጥበቃ የተሟላ የሚሆነው ሁለተኛውን ክትባት ከወሰዱ በኋላ ነው። ሁለተኛውን ዙር ለመውሰድ ሲመጡ የክትባት መዝገብዎን ይዘው ይምጡ። **የመጀመሪያውን ዙር ሲወስዱ ጎጂ ጎኖች አጋጥመዎት የነበረ ቢሆንም ሁለተኛውን ዙር መውሰድዎ በጣም አስፈላጊ ነው።**

# ጥያቄዎች ካሉኝ ማንን ነው የምገናኘው?

ጥያቄ ካልዎት የሕክምና አገልግሎት ሰጪዎን ወይም ክትባቱን የሚሰጥዎትን ሰው ያነጋግሩ።